# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት</u>?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል ዘጠኝ (ከክፍል ስምንት የቀጠለ)፤-...</u>***

በዶክተር በዬነ ጴጥሮስ (ሐዲያ ብሔር ዴሞክራሲያዊ ድርጅት) ሰብሳቢነት፣ በአቶ ከበደ ገብራይ (ኢዴኃቅ) ምክትል ሰብሳቢነት እና በዶክተር ታዬ ወልደ-ሰማያት (የኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር) ፀሐፊነት የተመራውና ከታኅሣስ ፱ እስከ ፲፫/ ፲፱፻፹፬ ዓ/ም በተካሄደው የአዲስ አበባው "ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ ጉባዔ" ውሳኔ መሠረት በጉባዔው ላይ ከተሣተፉት ውስጥ ሰላሣ-አንድ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት በተገኙበት ታኅሣስ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፬ ዓ/ም የኢሰዴአኃ ምክር-ቤትን መመሥረታቸው ይታወቃል፡፡ ቆየት ብሎም ሰባት በአገር-ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች በአባልነት ምክር-ቤቱን ተቀላቅለዋል፡፡ ኢሰዴአኃ በንድፈ-አሳብ ደረጃ በሁለት ሣምንት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ ከአባል ድርጅቶች አንድ-አንድ ተወካይ የሚሣተፉበት የምክር-ቤት ጉባዔና በሣምንት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ በማድረግ የድርጅቱን የዕለት-ተዕለት ተግባራት የሚሠራ፣ የሚቆጣጠርና የሚያስፈፅም ሰባት አባላት ያሉት ሥራ-አስፈፃሚ አካል (ኮሚቴ)፣ እንዲሁም የፋይናንስ፣ የሕዝብ ግንኙነት፣ የውጭ ግንኙነት እና የሕግና-ደንብ አካላት (ኮሚቴዎች)፣ ከአገር-ውጭም ከዋናው ጽሕፈት ቤት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነትና ትሥሥር ያላቸው ቅርንጫፎች እንዲኖሩት ተደርጎ ነበር የተደራጀውና የተዋቀረው፡፡

ምክር-ቤቱ በዚኽ አደረጃጀቱና አወቃቀሩ ለጋራ ትግሉ ቀጣይነት አስተዋፅዖ ያደረጉ ቀደም-ሲል የተጠቀሱ ተግባራትን ያከናወነና በርካታ እቅዶችን አንግቦ የተንቀሳቀሰ ቢሆንም፣ ለአገራችን አዲስ የሽግግር ምዕራፍ ለማስጨበጥ የሚያስችል ሁኔታን ለማመቻቸት የተጣለበትን ታሪካዊ ኃላፊነት መወጣት እንዳልቻለ ይታወቃል፡፡ ያ ብዙ የተደከመበትና በጊዜው አሉ የተባሉ የፖለቲካና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማካተት ከውስጡም ሆነ በተለይ ከኢሕአደግ በኩል የተተበተቡ እክሎችን ተወጥቶ የተካሄደ፣ አገር-አቀፍና ዓለም-አቀፍ ትኩረትን የሳበና አዲስ ተስፋን ያጫረ፣ ለዚሁ ሰላማዊና ሕጋዊ ስብሰባ ተሳትፎ ከአገር-ውጭ የገቡ ተወካዮችን ለግፈኞች የእስር ሰለባ (*) እስከ-መዳረግ የደረሰ መስዋዕትነት የተከፈለበት ጉባዔ የመጀመሪያ ሁለት ግቦችን መምታቱ (ማለትም ከሞላ-ጎደል በታቀደው መልክ ጉባዔውን ማካሄድ መቻሉና አሰባሳቢ ድርጅት ፈጥሮ በመውጣት መቋጨቱ) ከፍተኛ ክንዋኔ መሆኑ እሰየው የሚያሰኝ መሆኑ አከራካሪ አይመስለኝም፡፡ በተጨማሪም ድርጅቶች በተበታተነ መልክ ሣይሆን የጋራ በሆኑ የአገርና የሕዝብ ዓይነታ ጉዳዮች ላይ ተሰባስበውና ተባብረው በጋራ መሥራታቸው ምን ያኽል ሕዝባዊ ድጋፍን እንደሚያስገኝና ለትግሉ ፈር መያዝ ቁልፍ አስተዋፅዖ እንዳለው ከዚያ ወዲኽ ለተደረጉ ተመሣሣይ ጥረቶች ጠቃሚ ትምሕርትን ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ቀደም-ሲል በተጠቀሱት ዋና ዋና እና መሠረታዊ ችግሮች ምክንያት ድርጅቱ (ኢሰዴአኃ) ተልዕኮውን በተጠበቀው መልክ መወጣት ሣይችልና ብዙም ሳይርቅ በአጭር ለመቀጨት በቅቷል፡፡

*<u>ሀ) አደረጃጀትና አወቃቀር፤-</u>* ቀደም-ሲል እንደተጠቀሰው በአዲስ አበባው "ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገር-አቀፍ ጉባዔ" አዘጋጁ ክፍሎች በኩል ያ አገር-አቀፍ ስብሰባ አዲስ የሽግግር ሂደትን ሁኔታ የሚያመቻች "የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አካል (ካውንስል)" መመሥ-

*(* 1) ለአዲስ አበባው አገር-አቀፍ የሰላማና እርቅ ጉባዔ ከውጭ ከሂዱትና አዲስ አበባ መግባት ከቻሉት የልዑክ አባላትና ረዳቶች ውስጥ ከኢዴኃቅ አቶ አበራ የማነ-አብ፣ አቶ መሥፍን ተፈራ፣ ወ/ሮ ገነት ግርማ፣ አቶ ገነነው አሰፋ እና አቶ ዓለማየሁ ደሬሳ፤ ከመድኅን አቶ ሥዩም ዘነበ፤ ከኦነግ አቶ ኢብሳ ጉተማ በቀጥታ ከአየር ማረፊያ ወደ እስር ቤት የተወረወሩ ሲሆን፣ ሌሎቹ ሲለቀቁ አቶ አበራ የማነ-አብ እስካሁን በግፍ እንደታሰሩ ይገኛሉ)፡፡*

ረትና ለትግሉ የተሰባሰበ አቅጣጫ መስጠት እንደ ጉባዔው የቅርብ ጊዜ-ግብ ተይዞ እንደ-ነበር ይታወቃል፡፡ ለዚኽ የቅርብ-ጊዜ ግብም ምክር-ቤቱ የአጭር ጊዜ መርኃ-ግብሩን ነድፎ እንቅስቃሴ ማድረጉ አይዘነጋም፡፡ የኢሰዴአኃን ምክር ቤት የመሠረተ ጉባዔ አዘጋጅ አካል መኻል በአዲስ አበባው አገር-አቀፍ ጉባዔ ላይ መሣተፍ ስለሚችሉ ድርጅቶች ቀደም-ሲል የአሣብ ልውውጥ፣ ውይይትና ክርክር እንደተደረገ ግልጥ ነው፡፡ በዚኽ ጉዳይ ላይ አዘጋጅ ኮሚቴው በሰኔ ወር ሰማንያ-አምስት ዓ/ም ባደረገውና በቀጣይ ስብሰባዎቹም ላይ በዝርዝር ተወያይቶበታል፡፡ በመሆኑም በጉባዔው ላይ ሊሣተፉ የሚችሉ ድርጅቶችን በሦስት ከፍሎ፣ ማለት አንደኛ በሰኔ ወር ሰማንያ-ሦስት ዓ/ም የአዲስ አበባ የኢሕአዴግ ጉባዔ ላይ ተካፋይ የነበሩ፣ ሁለተኛ በፓሪሱ 'ሰላምና እርቅ በኢትዮጵያ አገራዊ ጉባዔ' ላይ ተካፋይ የነበሩ እና ሦስተኛ በነዚኽ በሁለቱ ያልነበሩ ሆኖም ድርጅታዊ ኀልውና ያላቸውና በተጨባጭ እንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ ከአገር-ውጭም ይሁን በአገር-ውስጥ ያሉ በሚል ፈርጆ ለማየት ሞክሯል፡፡ የሆነ ሆኖ በጉባዔው ላይ የተገኙት አርባ-አምስት ድርጅቶች የተለያዩ ተመክሮዎች፣ የአደረጃጀት ፈርጆች፣ ደረጃዎችና ያልተመጣጠኑ አቅሞች ያሏቸው እንደ-ነበር ይታወቃል፡፡ ከነዚኽ ውስጥ የፖለቲካ ድርጅቶችን በተመለከተ የተለያየና ያልተመጣጠነ ድርጅታዊ ልምድና ይዞታ የነበራቸው ሰባት ኅብረ-ብሔራዊ ድርጅቶች እና ሃያዎቹ የአካባቢ/ብሔረሰብ/የጎሣ ድርጅቶች ሲሆኑ የተቀሩት የሙያና የልዩ ልዩ የወል-ጥቅም-አስከባሪ ድርጅቶች፣ ስብስቦችና ቡድኖች ነበሩ፡፡ የኢሰዴአኃ አባላት ስብጥርና ይኽን ስብጥር ያንፀባረቀ ዝርግ አደረጃጀትና አወቃቀር ለምክር-ቤቱ ተልዕኮ ግብ አለመምታት ቀጥተኛ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡

አንደኛ ምንም እንኳን ጉባዔው የተለመውን ትርጉም ያለው አዲስ የሽግግር ሂደትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚደረገው ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ብሔራዊ-መግባባትን የሚጠይቅና ለዚኽም ሁሉንም ኃይሎች (የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ፣ የሙያና የልዩ ልዩ የወል ጥቅም-አስከባሪ ስብስቦችና ቡድኖችን) ማካተቱ ተገቢ ቢሆንም፣ ስብስቡ ወሳኝ ትግል ለማድረግ ሁኔታው የግድ የሚጠይቀውን ጠንካራ ማዕከል አልፈጠረም፣ አልነበረውምም፡፡ ትግሉ እንዲሰምር ለውጥ ፈላጊው ኃይል የሚከተለው የትግል ትልምም ሆነ ስልት የኢሕአዴግን ማንነት በትክክል ጠንቅቆ ማወቅ ላይ የተመሠረተና የሚጠይቀውን መስዋዕትነት በተገቢ ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ የአገሪቱ የወቅቱ ሁኔታ የሚጠይቀውን ወሳኝ ትግል ለማድረግ ደግሞ ቅድመ-ጉባዔ የትግሉን ልዕለ-ግብ በትክክል በተረዱ፣ ለዚሁ መተክል እውን መሆን በሚጠይቀው መራር ትግል ላይ እና የታለመውን ግብ መጨበጥ ያስችላል በተባለው የትግል ትልምና ስልት ላይ በተግባቡና በተማመኑ እንዲሁም ለትግሉ እርባና-ያለው አስተዋፅዖ ማድረግ በሚችሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መኻል ሙሉ መግባባት መኖሩ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ይኽንን ንድፈ-አሳባዊ ስምምነትና ሥነ-ልቦናዊ ዝግጁነት በተግባር ለመተርጎም የሚችል ጠንካራ ማዕከል ሊኖር የግድ ይላል፡፡

በእርግጥ ኢሰዴአኃን ከመሠረቱትና በአገር-ውስጥ “ሕጋዊነት” ኖሯቸው በግልጥ ይንቀሳቀሱ ከነበሩት አባል ድርጅቶች ውስጥ አገር-አቀፍ ከሆኑት ለምሣሌ የኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ኅብረት (ኢዴኅ) እና አካባቢ-ተኮር ከሆኑት መኻል የደቡብ ኅብረት ያ ስብጥር ስብስብ የተያያዘው ትግል ፈር እንዲይዝና ያመረረ ትግል ለማድረግ በጣም አስፈላጊ የሆነውን ማዕከላዊ ሚና መጫዎት ቢችሉ ምክር-ቤቱ የቆመለትን ዓላማ እግብ ለማድረስ የተሻለ ሁኔታን ሊፈጥር እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ሆኖም በሁለቱም በኩል ያንን ሚና መጫዎት እንዳይችሉ ያደረጓቸው የየራሣቸው ችግሮች ነበሯቸው፡፡ ኢዴኅ በምክር-ቤቱ መሥራች ከሆኑትና አባል ከነበሩት ውስጥ ነባርና አገር-አቀፍ ድርጅት ቢሆንም በወቅቱ ከሁለት ተከፍሎ አንደኛው አካል በውጭ ሌላው በ“ሽግግር” መንግሥቱ ውስጥ ተካፋይ ስለነበርና አመራሩ የኢሕአዴግ ይዞታ ላይ በግልጥ የሚታወቅ ልዩነት ያላስመዘገበ፣ እንዲሁም የትግሉ ልዕለ-ግብ፣ ትግልም፣ ስልትና አካሄድ ላይ ከጥንስሱ ተካፋይ ያልነበረ በመሆኑ ብቃት ባለውና በሌሎች ዘንድ ዓመኔታን ባሳደረ ሁኔታ ለትግሉ ማዕከል መሆን እጅጉን እንደሚሣነው የታወቀ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት እስከ አሥራ-ስድስት የብሔረሰብ ድርጅቶችን አቅፎ በነበረው የደቡብ ኅብረት በኩል ደግሞ የአደረጃጀት ተፈጥሮውና

አመራር ለመስጠት የሚጠበቅባቸው ግለ-ሰቦች በአቅም-ኮድኳጁና በአድማስ-ገዳቢው የጎሣ/ብሔረ-ሰብ ፖለቲካ ውስጥ እራሣቸውን በመቀየዳቸው ምክንያት ድርጅቱ ለትግሉ አገር-አቀፍ አመራር ለመስጠት የሚያስችል የማዕከላዊነት ሚና መጫዎት እንዳይችል ስንኩል አድርጎታል።

ከፖለቲካ ድርጅቶቹ በተመሣሣይ ሁኔታ ዋና ዋና ከሆኑት በልዩ ልዩ የሙያና የወል-ጥቅም-አስከባሪ ድርጅቶችና ስብስቦች መኻል እንዲሁ ጠንካራ የጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ማዕከል ሊኖርና በትግሉ ቀዳሚ ስልትና ሂደት ላይም አሻሚነት በሌለው ሁኔታ የጠራ ግንዛቤ ሊጨበጥና ሙሉ ስምምነት ላይ ሊደረስ ይገባል። በእርግጥ በወቅቱ በቂ እግር-ተከል የሆኑና ሠፊ መሠረት ያላቸው የሙያና የሲቪክ ማኅበራት አልነበሩም ሊባል ይችላል። ሆኖም እንደ ኢትዮጵያ መምሕራን ማኅበር፣ የነፃ-ጋዜጠኞች ማኅበር፣ ወዘተ.. የመሣሰሉት ድርጅቶች በቀላሉ ሊታዩ ወይም ቁልፍ ሚናቸው ዝቅ ተደርጎ ሊታይ አይችልም። ሕዝባዊ ትግሉ እንዲሰምር ደግሞ በእነኝኽ ሁለት የትግል አጋር ክፍሎች (የፖለቲካውና ፖለቲካዊ ያልሆኑት) መኻልም ሲሆን በልዕለ-ግቡ ላይ ቢያንስ ግን በቅርብ-ጊዜ ግቡ ላይና ያንን ለማስጨበጥ በሚያስችለውና መከተል በሚገባው የጋራ ትግል ስልት ላይ ግልጥና የማያሻማ መግባባት ሊኖር ይገባል። የሁለቱ ማዕከሎችም ሥራቸውን ለማቀናጀት የሚያስችሉ መንገዶችን በግልጥ በማወቅ፣ መናበብ በመቻልና ጥረታቸውን በማስተባበርና በማቀናጀት ሕዝባዊ ትግሉን ጎን-ለጎን ሆነው በአንድ አቅጣጫ በመግፋት የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚችሉበት ሁኔታ በቅድሚያ ሊነደፍ ተገቢ ሊሆን ይገባል። ሆኖም እነኝኽ አስፈላጊ ቅድመ-ሁኔታዎች በአማራጭ ኃይሎችም ሆነ ከዚያ በፊትና ከዚያም ወዲኽ በተፈጠሩ የጋራ ትግል መድረኮች (ምናልባት በተወሰነ ደረጃ ከኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት በስተቀር) ተግባራዊ መሆን ቀርቶ በሁሉም ኃይሎች ዘንድ በቅጡ የታሰበባቸው አይመስልም።

*ሁለተኛ* ኢሰዴአኃ በውስጡ ያቀፋቸውን ድርጅቶች በሙሉ አባልነትና በተባባሪ-አባልነት የፈረጀ ቢሆንም ቅድመ-ጉባዔም ሆነ በጉባዔው ላይ እንዲሁም ድኅረ-ጉባዔ በአንድ በኩል ከአገር-ውጭ እና በአገር-ውስጥ ባሉ አባል የፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሌላ በኩል አባል በተባሉትና ተባባሪ-አባል በተሰኙት መኻል መኖር የሚገባው ዝምድና፣ ትሥሥርና ኃላፊነት ላይ በሁሉም ዘንድ የጠራ ግንዛቤና መግባባት ነበር ማለት አይቻልም። ኢሰዴአኃ ያቀፋቸውን ኃይሎች በጅምላ እንደ-ያዘ ሊቀጥልም ሆነ እንዲሁ በሂደትና እንደ-ሁኔታው እንዳመቸ ቅድመ-ጉባዔ መግባባት ላይ ባልተደረሰበት መልክ አዳዲስ የትሥሥርና የዝምድና ክሮች በመፍተል የጋራ ትግሉን መምራት የማይሆን፣ ቢያንስ በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ እንደነበር አልተጤነም። ያም በመሆኑ በአገር-ውስጥም ሆነ ከአገር-ውጭ በተቃዋሚው ጎራ ተሰልፈው የሚገኙ ድርጅቶችን ቀጣይነት ባለው መንገድ በአንድ አደረጃጀት ሥር ማሰባሰብ፣ ማቆየትና በአንድ-አፍ ለመናገር እንደ-አንድ አካል ሆኖ ለመንቀሳቀስ አልተቻለም።

*ሦስተኛ* ከፍ-ሲል እንደተጠቀሰው ኢሰዴአኃ "የምክር-ቤት ጉባዔ፣ የሥራ-አስፈፃሚ ኮሚቴ፣ ወዘተ..." በሚሉ አዘቦታዊ ድርጅታዊ አወቃቀር እንደ-ተዋቀረ ቢታወቅም 'አባልና ተባባሪ-አባል' የተባሉት እንዲሁም ከአገር-ውጭ የሚገኙ ድርጅቶች በነዚኽና በሌሎቹ ውሳኔ-አስፈፃሚ ብቻ ሣይሆን ውሳኔ-ሰጭ አካሎች ውስጥ የሚኖራቸው ሚናና ተጠያቂነት-ያለው ኃላፊነት በተገቢ ስምምነት ያልተደረሰባቸውና በውል ተለይተው የተቀመጡ አልነበረም። ያም በመሆኑ ለምክር-ቤቱ ምሥረታ ደፋ-ቀና ያሉና ለተልዕኮው መሣካትም ሙሉ ኃይላቸውን በመስጠት የሚቻላቸውን ያደረጉና ለማድረግ ቆርጠው የተነሱ ድርጅቶች ሣይቀሩ በኢሰዴአኃን ይዞታ ላይ አመኔታቸው እየቀነሰ በመሄዱ የሚያደርጉትን ተሣትፎ ለመቀጠል አደፋፋሪ ሆኖ ስላላገኙ፣ የነበራቸው አስተዋፅዖም እየተዳከመ እንዲሄድና ምክር-ቤቱም በስም ብቻ ያለና እርባና-ቢስ ወደመሆን ደረጃ እንዲደርስ አድርጓል።

አራተኛ በአገራችን በሰፈነው ኢሕአዴግ-አመጣሽ የፖለቲካ አደረጃጀት ዘይቤ ምክንያት በመስክ ላይ የነበረው ጭብጥ ማንኛውም መሠረተ-ሰፊ የኃይሎች መሰባሰብን የሚሻ ክፍል የግድ ከሚገጥመው ሁኔታ አማራጭ ኃይሎች ሳይነካ ሊያልፍ ስለማይችል፣ ምክር-ቤቱ የተለያዩና አልፎም በተቃርኖ የተሞሉ ፖለቲካዊ አስተሳሰቦችንና አመለካከቶችን የሚከተሉ፣ የማይጣጣሙ ልዕለ-ግቦችን ያነገቡና በተለያዩ የአደረጃጀት ፈርጆች የተሰለፉ ድርጅቶችን ያቀፈ ነበር። ያ ዓይነት መሰባሰብ ደግሞ የሚጠበቀውን ያኽል በአባል ድርጅቶችና በማዕከላዊ አመራሩ ዘንድ አመኔታ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ትሥሥር እንዲኖር፣ ለጋራ ውሳኔዎች ተገዥ ለመሆንና ድርጅታዊ ሥነ-ሥርዓትን የጠበቀ ግንኙነትና የጋራ ኃላፊነትን ለመወጣት የሚያስችል ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ ነበር፣ ነውም። በመሆኑም ምክር-ቤቱም እንደ-ድርጅትም ሆነ አመራሩ ስብስቡን በአንድ የተተለመ የትግል መሥመር ለማስኬድ፣ ከኢሕአዴግ ጋር ጠንክሮ ለመደራደርም ሆነ አባላቱ በማዕከሉ ላይ አመኔታን ባሳደረ መልክ የተቃዋሚው ጎራ ወኪልና ልሣን መሆን አላስቻለውም። ያም ኢሰዴአኃ በኢሕአዴግ እንዲሰርጅና በመኻሉ ያሉ የአስተሳሰብና የአመለካከት ልዩነቶችን መሠረት ላደረገ ክፍፍል በር የከፈተ ነበር። ይኸ ደግሞ በአገር-ውስጥ በሚገኘው ዋናው ጽሕፈት-ቤት ብቻ ሣይሆን የአማራጭ ኃይሎችን ቅርንጫፍ ጽሕፈት-ቤቶች ለማቋቋም በተደረጉ ጥረቶች የገጠመ እክል ነበር። ለምሣሌ የሰሜን አሜሪካውን የኢሰዴአኃን ቅርንጫፍ በተቃዋሚው ጎራ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶችና ደጋፊ አካላት ሁሉ በተካተቱበት መልክ እንዲቋቋም በተደረገው አድካሚ ሂደት አንዳንድ ድርጅት አርቆ-ባላዬና በውሃ-ቀጠነ የጀመሩትን መተባበር ሲያቆሙም ሆነ ለአንዳንዶች ደግሞ ጨርሶ ላለ-መተባበር ሲቀርቡ ከነበሩ ምክንያቶች ውስጥ የኢሰዴአኃ አንዳንድ አባል ድርጅቶች ያላቸው አቋም "ከወያኔ ያልተሻለ" እና "በአገራዊ አንድነት ላይ አጠያያቂ"፣ ወዘተ፣... የሚሉ ይገኙበት እንደ-ነበርና ያም የጋራ እንቅስቃሴው በጎለበተ መልክ እንዳይቀጥል እክል እንደ-ፈጠረ፣ ለግንኙነቶች መሻከርና ለባሰ አለመተማመን በር እንደ-ከፈተ ይታወቃል። ይኸ በድርጅቶች መኻከል የነበረ እርስ-በርስ የመጠራጠር አባዜም ሁሉንም ድርጅቶች አካትቶ የጋራ እንቅስቃሴ ለማድረግ የሚጠይቀውን ቢያንስ መለስተኛ መተማመን ላይ የተመሠረተ የቅርብ ትብብር እንዳይኖር ሰበብ ሆኗል ማለት ይቻላል።

በነዚኽ ከዚኽ በላይ በተጠቀሱ ችግሮች፣ በወቅቱ በአገር ውስጥ በሰፈነው ጫና-አሣዳሪ ሁኔታ፣ የውጭ ኃይሎች ለአዲሶቹ ገዥዎች ባሳዩት ሚዛኑን የሣተና እንበለ-ማጠየቂያ ጭፍን ድጋፍ፣ እንዲሁም በሌሎች ተዛማች ምክንያቶች ሣቢያ ምክር-ቤቱ የተተለመውን የአጭር-ጊዜ መርኃ-ግብር ተከትሎ እንደታቀደው ሌላ ሁሉን-አቀፍ የሰላምና እርቅ ጉባዔ በአፋጣኝ ማድረግም ሆነ የተቃዋሚው ትግል በአንድነት እንዲቀጥልና ትርጉም ያለው ውጤት እንዲያስመዘግብ ማዕከላዊ አመራር መስጠት አልተቻለውም። ኢሕአዴግም በለጋው ምክር-ቤት የሚሰነዘሩ መጋተሮችን በቀላሉ ስላላያቸውና ጊዜ ከተሰጠው አደጋ ሆኖ ስለታየው፣ ኢሰዴአኃን በአጭር ለማስቀረት ወስኖ ለማፈራሰስ በመንቀሳቀሱ፣ በተለይም እራሱን "ከሽግግር-መንግሥትነት" ወደ-ቋሚ መንግሥትነት ለማሽጋገር ደፋ-ቀና የሚልበትና ከተቃዋሚው ጎራ የቻለውን ያኽል ለማስከዳት ጥረት የሚያደርግበት ጊዜ ስለነበርና ለዚኽ ደግሞ የምክር-ቤቱ አወቃቀር በአባላቱ መኻል ቅራኔዎች እንዲሰፉ በር የከፈተ በመሆኑ፣ በምክር-ቤቱ አባላት መኻል አለመተማመን እየጨመረና መፈራቀቁ እያየለ ልዩነቶችም እየተበራከቱና እየከረሩ እንዲሄዱ፣ በዚያው ልክ የኢሰዴአኃ እርባና እየኮሰሰ እንዲሄድና አብሶም ጓልውናው ጥያቄ ውስጥ እንዲገባና የፖለቲካ ሰመመን ላይ እንዲገኝ አስተዋፅዖ ማድረጉ አልቀረም።

ከሌሎቹ መሠረታዊ ችግሮች ጋር ተዳምሮ የኢሰዴአኃ አደረጃጀትና አወቃቀር ሌሎችን ወደሱ መሳብ ቀርቶ የታቀፉት ድርጅቶች ሥነ-ሥርዓት ተከትለውና ኃላፊነታቸውን አውቀው የምክር-ቤቱን ተልዕኮ በተግባር ለመተርጎምና ግዴታቸውን ለመወጣት አስገዳጅነት ያለው ሆኖ አልተገኘም። በመሆኑም፣ ምንም እንኳን .....

*በክፍል አሥር ይቀጥላል........*